# ጾም

## የጾም ትርጉም፡-

ለተወሰነ ጊዜ እህል ከመብላትና ውኃ ከመጠጣት መታቀብ ወይም ለተወሰኑ ወራት ከጥሉላት፣ ከሥጋ፣ ከቅቤ፣ ከወተት፣ ከእንቁላል፣ በአጠቃላይ ከእንስሳት ውጤት መከልከል ነው። ይህ ብቻ ጾምን ፍጹም ለማያደርግ ቅዱስ ያሬድ ሕዋሳት ሁሉ በየራሳቸው ክፉ ከመሥራት መጠበቅ አለባቸው ብሎአል። ይኸውም ዓይን ክፉ ከማየት ጆሮ ክፉ ከመስማት፣ምላስ ክፉ ከመናገር ይከልከሉ። በተጨማሪም አእምሮን ጉድተው ሰውን አሰክረው የማይገባ ከሚያሠሩና ከሚያሳስቡ የአልኮል መጠጦችም መጠበቅ እንዳለብን ማወቅ ይገባናል።

## የጾም ጥቅሙ፡-

የሥጋን ምኞት የምታጠፋ (የኃጢአት ምኞት ማለት ነው) የነፍስን ቁስል የምታደርቅ ለጉልማሶችም ጸጥታንና ርጋታን የምታስተምር፣ ከእንስሳዊ ግብርና ጠባይ የምትከለክልና ሰው መላእክትን መስሎ የሚኖርበት ደገኛ ሥርዓት ነች።

በብሉይ ኪዳን ብዙዎች በጾም ተጠቅመዋል። እግዚአብሔር የጾምን ሥርዓት የደነገገው ገና ከጠዋቱ አዳምን በፈጠረበት ወቅት ነው። «ዕፀ በለስን አትብላ» ማለት ትእዛዝ ቢሆንም ትእዛዙ የጾም ትእዛዝ መሆኑ ከማንኛችንም የተሰወረ አይደለም። አዳምና ሔዋን ይህን የጾም ሥርዓት በመሻር ዕፀ በለስን በልተው በመገኘታቸው ምን እንደ ደረሰባቸው ማንኛችንም በቅዱስ መጽሐፍ ላይ የምናነበው ነው።
በጾም የተጠቀሙ ቅዱሳን አበው ጾምን የጸሎት እናት የእንባ ምንጭ፣ የጽድቅ መሠረት በማለት ደገኛዋን ሥርዓት በተዋቡ ቃላቶች ከሸነው ሲያቀርቡአት፤ ዲያብሎሳዊ ትምህርት ያደረባቸው ደግሞ «ወደ ሆድ የገባ አያረክሰም ከአፍ የሚወጣ ስድብ ምንዝርነት ግን ያረክሳል» ነው ያለው መጽሐፉ እና ጾምን አልጾምን ለመንፈሣዊ ሕይወታችን የሚሰጠው ረብ የለም ሲሉ ይሰተዋላሉ።

በመሠረቱ ይህን ቃል ጌታ ተናገረው ለጾም አለመሆኑን ማቴ.15፡1-20 ብቻ ማንበቡ በቂ ቢሆንም ለእነዚህ ሐሰተኞች ማሳፈሪያ ይሆን ዘንድ ሌሎች ጥቅሶችንም አክለን እናቀርብላቸዋለን። በዚያን ጊዜ የነበሩ አይሁድ ጌታ ይህን ቃል ሲናገር በሰሙ ጊዜ እንደ አሁኖቹ የጾም ጠላቶች ሁሉ ልባቸው ጠማማ ነውና አጣመው ተርጉመውት ሲያጉረመርሙ ሐዋርያት በመስማት «በዚህ ቃል እንደተሰናከሉ» አውቅህን? ሲሉት ጌታ ግን የተናገረው ቃል የሚያሰናክል ስላልነበረ «ተውአቸው አባቴ ያልተከለው ተክል ሁሉ ይነቀላል፣ እውርን እውር ቢመራው ተያይዘው ገደል ነው» ብሏል የዛሬዎቹም ዓይን ልቦናቸው የታወረ ሆነው ባለ ሌሎችንም እንምራ በማለት ወደ ገደል ይዘዋቸው ሲገቡ ይታያሉ።

ጌታ ግን ደቀመዛሙርቱ የዚህን ምሳሌ ትርጉም ንገረን ባሉት ጊዜ «እጅን ታጥቦ መብላትና አለመብላት ሰውን ከሃይማኖት አያወጣውም ወይም አያረክሰውም፤ ክፉ መሥራትና መናገር እንጂ» ብሎ እጅን ታጥቦ ስለመብላትና ስለ አለመብላት መናገሩን ግልጽ አድርጎ አሰቀምጦታል። እኑ ሆድ አምላካ[illegible]ውሉት ዘንድ እንመክራቸዋለን።

www.ethiopianorthodox.org

# ጾም በብሉይ ኪዳን

ጾም በሕዝብ ላይ የተቃጣውን መከራ ለማቅለል ይረዳል። ለዚሁም በማስረጃነት የሚጠቀሱ አያሌ ጥቅሶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በፍረው እናገኛለን። ኢያሱ እስራኤላውያንን እየመራ ወደ ተስፋይቱ ምድር በሚገቡበት ጊዜ ኢያሪኮን በቁጥጥር ሥር ካደረጉ በኋላ ጋይ የተባለችውን ከተማ ለመያዝ በሚነሳሱበት ወቅት ከዚያ በፊት በእስራኤል ሰልፍኞች ዘንድ ያልታየ የመሸሽ የመፍራት ስሜት ተንጸባረቀ። ከሰልፈኞቹም 36 ሰዎች በጠላት ተመተው ወደቁ። ኢያሱም ስለደነገጠ ልብሱን ቀድዶ በታቦተ ሕጉ ፊት እስከ ሰርክ በግንባሩ ወድቆ በጾም ዋለ። በዚያን ግዜ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል በደል የፈጸሙ እንዳሉ ነግሮት አጥፊዎችን ቀጥቶ ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቋል። መጽሐፈ ኢያሱ7፤6-9

በአንድ ዘመን የጊብዓም ሰዎች በአንድ ሌዋዊ ሰው ሚስት ላይ እንደ ውሻ በመፈራረቅ የማይገባ አስጸያፊ ድርጊት ሲፈጽሙባት ስለደሩ ቧት ላይ ምታ ያገኛታል። እርሱም ይህን በደሉን ለወገኖች ለማለጥ የሚስቱን አካላት ቆራርጦ ወደ እስራኤል ርስት (አገር) ሁሉ ፍረዱኝ ብሎ ሰደደ። የእስራኤል ልጆች በዚህ ተቆጥተው አራስ ነብር ሆነው ወደ ብንያም ልጆች ይህን እኩይ ምግባር ያደረጉትን የጊብዓም ሰዎች አሳልፈው እንዲሰጡአቸው መልእክት ይልካሉ። የብንያም ልጆች ግን ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ። በዚህ የተነሣ በእስራኤል ልጆችና በብንያም ልጆች መካከል ጦርነት ተከፈተ። የእስራኤል ልጆች አራት መቶ ሺህ ጦር አሰለፉ፤ የብንያም ልጆች 26 ሺህ ሰባት መቶ ጦር አሰለፉ። ይሁን እንጂ የእስራኤል ልጆች በቁጥር እጅግ ከፍተኛ ቢሆኑም ሁለት ግዜ በብንያም ልጆች ድል ተደረጉ። ከመካከላቸውም ብዙ ወገኖቻቸውን አጡ። ለሦስተኛውም በጾም ወደ እግዚአብሔር ጮሁ እግዚአብሔርም ረዳቸው፤ የድል ግዳይ ለእነርሱ ሆነ።

እኛም ዛሬ እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደ ባሕር አሸዋ ከበዙ ሰራዊተ አጋንንት ጋር በዚህች ምድር ላይ ጦርነት ገጥመናል፤ ሰራዊተ አጋንንት ቢያሸንፉንም እኛ ግን በጾም በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ከጮህን የማታ ማታ ድል የክርስቲያኖች መሆኑን ባለመጠራጠር በጾም በጸሎት ወደ እግዚአብሔር መውደቅ አለብን።

ከሕንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ በ127 አገሮች ላይ የነገሰ አርጤክስስ የሚባል ንጉሥ ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር። በሚገዛቸው በ127 አገሮችም ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጎ የሾመው ሐማመርዶኪዮስ የተባለ አይሁዳዊ ለምን አልሰገደልኝም በሚል ቂም ተነስቶ በአጠቃላይ በ127 አገሮች ያሉ አይሁዳውያን እንዲፈጁ ትእዛዝ አስተላለፈ። ሐመርዶኪዮስ ግን የንግሥቲቱ የአስቴር አጐት ነበርና ወደ እሷ ዘንድ ይህ በወገኖችሽ ላይ የተቃጣውን የሐማን ሰይፍ ወደ ንጉሡ ዘንድ ገብተሽ በመንገር ልታስቆሚ ይገባል ይላታል። አስቴርም ነገደ ይሁዳ ሁሉ በጾም በጸሎት ያስቡኝ ዘንድ መልእክት አስተላለፉ፤ በንጉሡ ዘንድ ባለሟልነት አገኝ ዘንድና የሐማን ነገር አፈርስ ዘንድ ስላለች፤ በአጠቃላይ በ127 አገር ተበትነው ያሉ አይሁዳውያን ለሦስት ቀንና ሌሊት ጾምና ጸሎት ያዙ። በመጨረሻም ሐማ በቆፈረበት ጉድጓድ ገባ።አይሁዳውያን ግን ከተቃጣባቸው ሰይፍ በጾም ምክንያት ዳኑ። ይህንን ከእኛ ሕይወት ጋር እናገናኘበው፤ መጽሐፈ አስቴርን በሙሉ ይመልከቱ፤ በተለይ ም.4፤16።

እግዚአብሔር በነነዌ ከተማ ላይ ፈርዶ በእሳት ሊያጠፋት ካሰበ በኋላ የነነዌ አገር ሰዎች ከንጉሡ ጀምሮ እስከ ተራው ሰው ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት በጾም ቢለምኑ ምሯቸዋል። ትንቢተ ዮናስን በሙሉ ይመልከቱ።

ዳዊት አርዮንን በማስገደሉ በደል ስላደረገ በነቢዩ ናታን ግሳጼ ሰባት ቀን በጾም በጸሎት ውሏል፤ መጽ.ሳሙኤል ካልዕ 12፤17። ነቢዩ ሙሴ አንድ ጊዜ ሕግ ለመቀበል፤ ሁለት ጊዜ እስራኤልን በበደላቸው ምክንያት ከእግዚአብሔር ለማስታረቅ አርባ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከምግብ በመለየት ከእ[illegible] www.ethiopianorthodox.org ኦሪት ዘዳግም 9፤9-18 እና ምእራፍ 10፤10።

ነቢዩ ኤልያስም ከኤልዛቤል ተጣልቶ ወደ ኮሬብ በሸሸ ጊዜ በመንገድ ደክሞት ከክትክታ ዛፍ ጥላ ሥር ዓረፈ፤ ወዲያውም እንቅልፍ እንቀላፋ። የእግዚአብሔር መልአክ መጥቶ ቀሰቀሰው ቢነቃም ከራስጌው መብል መጠጥ አገኘ፤ በልቶ ጠጥቶ ጉዞውን ጀመረ። ከዚያም በኋላ አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት እስከ እግዚአብሔር ተራራ ድረስ ያለ ምንም ምግብ ተጓዘ፤ 1ኛ ነገሥት 19፥6-10።

- **ትንቢተ ኢዮኤል** 2፥14 «በጽዮን መለከት ንፉ፤ ጾምን ቀድሱ» ታዲያ ነቢዩ ጾምን ቀድሱ እያለ ሲነግረን የዛሬዎቹ እነሆድ አምላካቸው ጾም አያስፈልግም የሚሉት ከየት አምጥተው ይሆን?

-**መዝ.34(35)፥13** «ነፍሴን በጾም አደከምኋት» ዳዊት የጾምን አስፈላጊነት ሲገልጽ አየኸውን?

-**ትን.ዳን.10፥2** «በዚያም ወራት እኔ ዳንኤል ሦስት ሳምንት ሙሉ ሳዝን ነበርኩ፤ ማለፊያ እንጀራም አልበላሁም፤ ሥጋና ጠጅም በአፌ አልገባም» በጾም^ን ወቅት ሥጋ መብላት፤ ጠጅ መጠጣት እንደማይገባን ዳንኤል ነግሮናል።

-**መዝ.108፥24** «ጉልበቶቼ በጾም ደከሙ፤ ሥጋዬም ቅቤ በማጣት ከሳ» ከቅቤ መጾም እንዳለብን ዳዊት ነገረን።

አንዳንድ ሰዎች የጾም ጊዜ ለምን ይወሰናል፤ ሥጋ ቅቤ የመሳሉትስ ለምን ጾም ሆኑ? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዚህ ቀን ጹሙ፤ ከእነዚህ ከእነዚህ ጹሙ የሚል የለም ይላሉ መጾም አስፈላጊ መሆኑ ከተመነበት ሕግና ሥርዓት ቤተ ክርስቲያን አውጥታ በዚህ ቀን ጹሙ ብትለን የሚያስነቅፋት አይደለም፤ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን አባቶች ሙሉ ሥልጣን ሰጥቶአቸዋልና። «እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል» ማቴ.18፥18 ብሎ ይህን አማናዊ ቃሉን የተናገረው ለሐዋርያትና እነርሱን መስለው እስከ እለተ ምጽአት ቤተ ክርስቲያንን ለሚመሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ዋቢ አድርገው በሚደነግጉት ድንጋጌ ባንመራ አመጸኞች ነን። ክርስቶስም «ጌታ ሆን ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም፤ ትእዛዜን የሚያከብር እንጂ» ብሎ አስቀድሞ የተናገራትን ሁሉ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለብን አስጠንቅቆናል፤ በትዕቢታችን እነሱም ሰው፤ እኛም ሰው እነሱ ባወጡት ሕግ አንመራም የሚሉ ከሆነ፤ «በዚያን ጊዜ ጌታ ሆይ በስምህ አጋንንትን አላወጣንም? በስምህስ ብዙ ድንቅ ሥራዎችን አላደረግንምን? ይሉኛል፤ እኔ ግን እናንተ አመጸኞች ከእኔ ሂዱ ብዬ እፈርድባቸዋለሁ» ሲል ማቴዎስ 7፥22-23 ላይ ተገልጿል። ስለዚህ አመጸኝነት አያዋጣም። «በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተ ጳጳሳት አድርጎ ለሾመበት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ» የሐዋ.ሥራ20፥28። ይህን የመሰለ ሃላፊነት የተሰጣቸውን የአባቶችን ትእዛዝ መናቅና አለመቀበልን የመሰለ አመጽ ከዬት ይኘል?

## ጾም በሐዲስ ኪዳን

የሐዲስ ኪዳን ጾም ከብሉይ ኪዳን ጾም የተለየ ነው። በብሉይ ኪዳን ያለው ጾም ሥጋዊ ችግርን የሚመለከት ሲሆን፤ በሐዲስ ኪዳን ግን የሚጾመው ለጽድቅ ነው። ይኸውም ለእግዚአብሔር ተብሎ ነው ማለት ነው፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሥራው መጀመሪያ ያደረገው ጾምን ስለሆነ መሥራቹ ራሱ ክርስቶስ ነው። የሚከተሉትን ጥቅሶች በሐዲስ ኪዳን ጾም እንደታዘዘ የሚያመለክቱ ናቸው።

-**ማርቆስ 9፥29** «በጸሎትና በጾም ካልሆ[illegible]ም» አጋንንትን ለማስወጣት ከእግዚአብሔር ኃይል ለማግኘት ጾም አስፈላጊ መሆኑን ጌታ ራሱ ተናግሯል፤
www.ethiopianorthodox.org

ማርቆስ 2፥20 «ሙሽራው ከእነሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል፤ በዚያ ወራት ይጾማሉ»፤ አለ እንጂ እኔ ጾሜላችኋለሁና መጾም አያስፈልጋችሁም አላለም።ስለዚህ ጌታ ጾሞልናል መጾም አያስፈልገንም የሚሉ ክፍሎች ምን ያህል የተሳሳቱ መሆናቸው በዚህ ይታወቃል። እንደዚህማ ቢሆን ኖሮ ክርስቶስ ስለ እኛ ጸልዮዋል እኛም መጸለይ አያስፈልገንም ነበር።

ማቴ.6፥16 «ስትጦሙም እንደግብዞች አትጠውልጉ» ማለቱ መጾም መንፈሳዊ ግዴታ መሆኑን መግለጹ አይደለምን? ጾም ለክርስቲያኖች ሕግ ባይሆን ኖሮ ስትጦሙ እንዲህ ሁኑ ብሎ ትእዛዝ ባልሰጠ ነበረ።

ሉቃስ 6፥21 «እናንተ አሁን የምትራቡ ብፁአን ናችሁ ትጠግባላችሁና» ብሎ ዛሬ ወደው ፈቅደው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ብለው የሚራቡ የሚጠሙ ኋላ በመንግሥት በማያት በተድላ ደስታ እንደሚኖሩ ራሱ ጌታ ተናግሯል።

የሐዋ.ሥራ13፥3 «ከጾሙ ከጸለዩ በኋላ...» ሲል ሐዋርያት ጌታ ጾሞልናል ብለው ከመጾም እንዳልተከለከሉና ይልቁንም እነሱም ለሥራቸው ሁሉ ጾምን መሠረት ያደርጉ እንደ ነበር ነው የምናየው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለጾም ሥርዓትና ደንብ አውጥታለች በዓመት ውስጥ ሰባት የአዋጅ አጽዋማት እንዳሉና ማንኛውም ክርስቲያን እነኝህን አጽዋማት እንዲጾም ታዛለች። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ. **ዓቢይ ጾም**

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኛ የጾመው ጾም ሲሆን፤ ለእኛም አርአያ የሆነበት ነው። ይህም በማቴ.4፤1-11 የተገለጸ ነው። ጌታ የጾመው አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ሲሆን እኛ ግን አሁን የምንጾመው 55 ቀናት ነው። ይህም በብዙዎች ዘንድ ሲተች ይሰማል። በመሠረቱ እንኳን 55 ቀን ዓመትም ብንጾም እግዚአብሔር በጸጋ ላይ ጸጋ ይጨምርልናል እንጂ አያስኮንንም። ዳሩ ግን ተጨማሪዎቹ አሥራ አምስት ቀናት የተጨመሩበት ምክንያት አለው።

አንደኛው ምክንያት በዓቢይ ጾም ውስጥ ስምንት ሳምንታት ይኖራሉ። ከነዚህም ቀኖች ውስጥ ሰባት ቅዳሜ። ስምንት እሁድ ይገኛሉ። እነዚህም አሥራ አምስት ቀናት ሲሆኑ ከጥሉላት እንጂ ከእህል ውኃ ስለማይጦሙ እነዚህ ቀናት ሲቀነሱ አርባ ቀን ይመጣል፤ ስለዚህ ተጨማሪዎቹ አሥራ አምስት ቀናት በዓቢይ ጾም ውስጥ ሳሉት ቅዳሜና እሁድ ምትክ የሚሆኑ ናቸው።

ዓቢይ ጾም የተባለበት ምክንያት የጌታ ጾም ስለሆነና ታላላቅ የሰይጣን ፈተናዎች ድል የተነሱበት፤ ዛሬም ክርስቲያኖች የጌታን አርአያ ተከተለው ሰይጣንን ድል የሚነሱበት ጾም ስለሆነ ነው። በሕዝቡ ዘንድ ሁዳዴ ይባላል፤ ሁዳዴ ማለት የመንግሥት መሬት፤ የመንግሥት ርስት ማለት ነው። የመንግሥት ሁዳድ በሚታረስበት ጊዜ አዝመራው በሚሰበሰብበት ጊዜ ልጅ አዋቂ ሳይባል የመንግሥቱ ዜጋ ሁሉ ለሥራ ታጥቆ እንደሚነሣ ይህንንም የጌታ ጾም የጌታ ሁዳድ የክርስቶስ ዜጎች የሆኑ ምእመናን ሁሉ ይጾሙታልና የሁዳዴ ጾም ተባለ።

2ኛ. **ጾመ ሐዋርያት**

ይህ ጾመ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው የወንጌልን መልእክት ለማዳረስ ወደ ዓለም ከመሰራጨታቸው በፊት አምላካቸውን አብነት በማድረግ የሥራቸው መጀመሪያ ያደረጉት ጾም ነው። መነሻው ከእለተ ጰራቅሊጦስ ማግሥት ሆኖ፤ በመጨረሻው ወይም መፈቻው ሐምሌ 5 ቀን ነው።



3ኛ. **ጾመ ድኅነት**

3ኛ. **ጾመ ሰብከት**
የክርስቶስን መምጣት የሚጠባበቁ አበው እነ ኢሳይያስና እነ ዳንኤልን የመሰሉት የጾሙት ሲሆን፤ ይኸውም ጾመ ነቢያት ተብሎ ይታወቃል። የጾሙ መጀመሪያ መንፈቀ ኅዳር ማለት የኅዳር እኩሌታ ሲሆን መጨረሻው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታኅሣሥ 29 ቀን ነው።

4ኛ. **ጾመ ፍልሰታ**
ይህን ጾም ለመጀመሪያ ጊዜ የጾሙት ቅዱሳን ሐዋርያት ሲሆኑ፤ በአሁኑ ጊዜ ግን ከሕጻን አንስቶ እስከ ሽማግሌ ድረስ የሚጾሙት ጾም ነው። የሚጀምረው ነሐሴ 1 ቀን ሲሆን፤ የሚያበቃው ወይም መፈቻው ነሐሴ 16 ቀን የእመቤታችን የትንሣኤና የእርገቷ መታሰቢያ በዓል ላይ ነው።

5ኛ. **ጾመ ድኅነት**
የረቡእና የዓርብ ጾም ነው። ከሌሎቹ እለታት ተለይተው ረቡእና ዓርብ የሚጾሙባቸው ምክንያት

- **ረቡእ**፦ የጌታ ምክረ ሞቱ ማለትም በአንድ ሰው ምክንያት የተነሣ ሕዝቡ ከሚታመስ አንድ ሰው ቢሞት አይጎዳምና ይሙት በቃ ብለው ተማክረው ሞቱን የፈረዱበት እለት ስለሆነ፤

-**ዓርብ**፦ ረቡእ ያጸደቁትን የይሙት በቃ ፍርድ በእለተ ዓርብ ተግባራዊ አድርገውታል። እኛም በነዚህ ቀናት በጾም በስግደት ስለ እኛ ሲል የሞተውን አምላካችንን እናስባለን። በዚህ ምክንያት ጾመ ድኅነት ይባላል።

6ኛ **የነነዌ ጾም**
መሠረቱ የነነዌ ሰዎች የጾሙት ጾም ነው። ዛሬም እኛ እንደ እነሱ በኃጢአታችን እንዳንጠፋ ጌታ ምህረቱን ይሰጠን ዘንድ የምንለምንበት ጾም ነው።

7ኛ **ጾመ ገሃድ**
ገሃድ የቃሉ ትርጉም መገለጥ መታየት ነው። በጥምቀት መገለጥ መባሉ ሰው የሆነው አምላክ በዓለም ሲኖር እስከ 30 ዓመት እድሜው ድረስ ሰዎችን ለማዳን የመጣ መሲሕ ሰው የሆነው አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ እሱ መሆኑን ሳያውቁ ከሆኑ በኋላ በ30 ዓመት እድሜው በባሕረ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ አብ በደመና ሆኖ «የምወደው ልጄ ይህ ነው» በማለቱ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በራሱ ላይ ሲያርፍ በመታየቱ ነቢያት ይወርዳል፣ ይወለዳል፣ ይሰቀላል፣ ይሞታል፣ ይነሳል ብለው የተናገሩለት መሲሕ እርሱ መሆኑ ተገልጦአልና፤ እንዲሁም ሦስቱ አካላት በአንድ ጊዜ ታይተዋልና ምስጢረ ሥላሴ የተገለጠበት በመሆኑ ገሃድ ይባላል። የገሃድ ጾም ጥር10 ቀን ለ11 አጥቢያ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

**ዓምደ ሃይማኖት ከሚለው ብርሃኑ ጎበና በ1992 ካሳተሙት የተወሰደ።**